# የትውልድ ውርስ

## ከመተሐራ እስከ ፓሪስ

(ከወጣት ፖለቲከኛነት እስከ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማትነት)



ደስታ መብራቱ

# የትውልድ ውርስ

## ከመተሐራ እስከ ፓሪስ

(ከወጣት ፖለቲከኛነት እስከ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማትነት)

**ደስታ መብራቱ**

**ሐምሌ 2015**

*© ደስታ መብራቱ ሐምሌ 2015 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

*የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው*

*All rights reserved*

*ለተጨማሪ መረጃ እና ተግባቦት: Dmebratu57@gmail.com*

ISBN 978-99990-50-57-9

## መታሰቢያነቱ

*ይህ መጽሃፍ ፍጹም በሆነ ቀና እምነት የብዙሃኑን ግፉዓን ጎስቋላ ኑሮ ከመሰረቱ ለመቀየር ውድ የሆነውን የወጣትነት ዕድሜአቸውን እና ህይወታቸውን ለሰጡት **'የእኔ ትውልድ'** አባላት ይሁንልኝ።*

**ምልከታ ከልጁ**

የዚህን መጽሃፍ ፀሃፊ የማውቀው ከልጅነቴ ጀምሮ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው ልጁ ስለሆንኩኝ ነው። ይህንንም እንደመታደል ነው የምቆጥረው። ነፍስ ከአወኩበት ጊዜ ጀምሮ በቅንነቱ፤በታታሪነቱ፤በመልካም አባትነቱ የማውቀው ሲሆን፤ ከየት እንደመጣሁኝ ለመረዳት ከእኔ መወለድ በፊት ስለነበራቸው የህይወት ታሪክ ለማወቅ ጥረት አደርግ ነበር። እድሜዬን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ስለ ቀድሞ ህይወታቸው፤ ከዛም ባለፈ ስለ አያቶቼ በተገኘው አጋጣሚ እያዋዛ ሲያጫውተኝ እንደ ተንቀሳቃሽ ምስል በምናቤ እየሳልኩኝ መዝናናት ልማዴ ነበር። ይሄም፣ የሰው ልጅ ከወላጆቹ ሊወርሳቸው ከሚችላቸው ነገሮች ሁሉ ቀዳሚ ቦታ ሊሰጠው ይገባል ብዬ ለማምነው ማንነቴ እና ላደረብኝ ብርቱ የሃገር ፍቅር መሰረት ሆኗል።

ቤታችን፣ እንግዳ፣ ወዳጅና ዘመድ የማይጠፋበት ቤት በመሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ወላጆቼ ከወዳጆቻቸው ጋር ስላለንበት ዘመን እና ስለ ሃገር ጉዳይ ሲጫወቱ የማዳመጥ፣ ከጊዜ በኋላም የጨዋታው ተሳታፊ የመሆን እድል ነበረኝ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ጭውውቶች "እንግዲህ ያለን ተስፋ መጪው ትውልድ ነው"፣ በሚል ሽንፈት አዘል መንፈስ ሲደመደሙ የሃዘን ስሜት ይወረኝ ነበር። ምክንያቴም፣ የምንመኛትን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጽኑና ንቁ ተሳትፎ ያስፈልጋል የሚል እምነት ስለነበረኝ ነው። በተለይ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ዉስጥ፣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና የተጫወተው፣በተለምዶ 'የ60ዎቹ ትውልድ' በመባል የሚታወቀው የወላጆቼ ትውልድ የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ በሚመለከት የበኩሉን ድርሻ ከመወጣት ይልቅ ይህንን ሃላፊነት በደፈናው ወደሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፉ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር። ከወላጆቼ ትውልድ፣ ከስህተቱም ሆነ ከመልካም ምግባሩ ብዙ ልንማር እንደምንችል ይሰማኛል። ኢትዮጵያም የሁላችንም ሃላፊነት ናት።

አባቴ ፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ ሃላፊነት ወስዶ 'የትውልድ ውርስ' በሚል ርእስ ይሄንን ስራ በማዘጋጀቱ በኔ ትውልድ ስም ከፍተኛ ምስጋና ከአክብሮት ጋር ላቀርብለት እወዳለሁ። የእርሱ የህይወት ጉዞ መታሰቢያ ሆኖ ከማገልገሉም ባሻገር፣ የተለያዩ እሴቶች እና ቁምነገሮችን ያዘለ ስራ በመሆኑ አንባቢው ጠቃሚ ሆኖ ያገኘዋል የሚል እምነት አለኝ። የዘመናችንን ችግሮች ከማተትም ባሻገር፣ ከራሱ ህይወት እና ከአገራችን ታሪክ ጋር በማያያዝ፣ የችግሮቻችንን ምንጮች ለይቶ ባልተወሳሰበ መልኩ ከመፍትሄ ጋር ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት እንዳደረገ ይሰማኛል። የዚህ ጥረት ውጤት ለእኔ ትውልድ ጠቃሚ ዘር በመሆን መልካም ፍሬ እንደሚያፈራ ተስፋ አደርጋለሁ።

**ዳግማዊ ደስታ መብራቱ**

## ማውጫ


ምስጋና
መቅድም 1
መግቢያ 3
**1. ቤተሰብ እና ልጅነት** 5
1.1 አባታችን እና ወላጆቹ 5
1.2 እናታችን እና ቤተሰቧ 9
1.3 አዋሽ እና ወላጆቻችን 11
1.4 መተሃራ እና ቤተሰባችን 14
**2. ዕድገት እና ትምህርት** 30
2.1 ትምህርት በመተሃራ እና አዋሽ 30
2.2 ትምህርት በናዝሬት 37
**3. ዘመቻ፣ ፖለቲካ፣ እና እስር** 48
3.1 ዘመቻ እና ፖለቲካ 50
3.2 ወጣት ፖለቲከኝነት 61
3.3 የላብ አደር ፖለቲከኝነት 64
3.4 የሙሉ ጊዜ ፖለቲከኝነት እና እስር 87
**4. ዩኒቨርሲቲ፣ ሥራ፣ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት** 116
4.1 ለዩኒቨርሲቲ ዝግጅት 116
4.2 ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 120
4.3 ሥራ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 131
4.4 ፍቅር እና ቤተሰብ ምስረታ 150
**5. ድህረ ምረቃ ትምህርት እና ስራ** 163
5.1 ለትምህርት ወደ ስዊድን 163
5.2 ከሉንድ መልስ በአዲስ አበባ 178
**6. ዲፕሎማትነት በናይሮቢ እና ፓሪስ** 184
6.1 አፍሪካ ቢሮ በናይሮቢ 184
6.2 ሥራ እና ኑሮ በፓሪስ 201
6.3 ሁለተኛ ዙር በናይሮቢ 213
**7. የትውልድ ውርስ እና ሃገር** 224
7.1 የምህዳራዊ ምልከታ አስፈላጊነት 225
7.2 የአዕምሮአዊ ውቅር ለውጥ 228
መደምደሚያ 239

## *ምስጋና*

*ይህ መጽሀፍ እኔ በሶስት ትውልዶች ያለፍኩባቸውን የፖለቲካ እና ሙያ ህይወት ጉዞ በመዳሰስ ለተተኪው ወጣት ትውልድ ተሞክሮ እንዲያካፍል ታስቦ የተጻፈ ነው። በወጣት ፖለቲከኝነቴ ወቅት እንደ ብዙዎቹ የስልሳዎቹ ትውልድ አባላት በርካታ የፈተና ወቅቶችን አሳልፌአለሁ። ከዚያ ፈታኝ ወቅት በህይወት ተርፌም በምወደው የሙያ መስክ በመሰማራት የአቅሜን ያህል ለሰው ልጆች ደህንነት የሚጠቅም አስተዋጽኦ ለማበርከት በቅቻለሁ። ለዚህም በቀዳሚነት እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በመቀጠልም፣ ማንነቴን በመቅረጽ ከፍተኛውን ድርሻ ያበረከቱትን ወላጆቼን አቶ መብራቱ በላይ እና እማሆይ ጽጌማርያም ነፍሳቸውን በአጸደ ገነት እንዲያኖርልኝ እመኛለሁ። በመቅድሙ ላይ እንደተጠቀሰው የአዲሱ ትውልድ አባል የሆነው ልጄ ዳግማዊ ደስታ መብራቱ እንደ ቀዳሚ ትውልድ ያለብኝን ሃላፊነት በመኮርኮር በጡረታ ዘመኔ ይህንን መጽሀፍ ለመጻፍ ስላነሳሳኝ ከልብ አመሰግነዋለሁ።*

*በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተለያየ የህይወት ዘመኔን የተጋሩ ቤተሰቦቼ፣ አብሮ አደጎቼ፣ የትምህርት ቤት ጓደኞቼ፣ የፖለቲካ ጓዶቼ፣ የስራ ባልደረቦቼ፣ የእውቀት እና ሙያ አባቶቼ ስም ተጠቅሷል። ላለፍኩበትም ሆነ ዛሬ ላለሁበት ደረጃ የእነኚህ ሰዎች አስተዋጽኦ በተለያየ መልኩ ከፍተኛ በመሆኑ ከወገቤ ጎንበስ ብዬ ክብረት ይስጥልኝ እላለሁ። ፈተና በበዛበት የወጣት ፖለቲከኛነት ዘመኔ ከጎኔ የቆሙትን ብቻ ሳይሆን ፈተና ሲያወርዱብኝ የነበሩትንም፣ ስማቸው ባይጠቀስም፣ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ምክንያቱም፣ ያለፍኩባቸው ፈታኝ ሁኔታዎች በሙሉ ከሌላ ቦታ ላገኛቸው የማልችላቸውን ክህሎቶች እና ተሞክሮዎች ሰጥተውኛልና። በመጨረሻም፣ ረቂቅ መጽሃፉን አንብበው ጠቃሚ አስተያየት እና ግብዓት ለሰጡኝ ለአቶ ማሞ ደስታ፣ አቶ ታደሰ ከበደ፣ ዶ/ር ፀጋዬ ከበደ፣ አቶ ሙሣ ዓሊ፣ አቶ ታደለ መብራቱ፣ ወ/ሪት ፍሬስም መብራቱ፣ አቶ ግርማ በቀለ፣ ዶ/ር ጉልላት ከበደ፣ አቶ ቴዎድሮስ በላይነህ፣ አምባሳደር አረጋ ኃይሉ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው እንግዳ እና ፕሮፌሰር ዮናስ እንዳለ ገዳ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።*

## መቅድም

በጥቅምት ወር 2015 ዓም፣ ጆሃንስበርግ ደቡብ አፍሪካ የሚኖረውን ልጄን ዳግማዊ ደስታ መብራቱን ለመጎብኘት ወደዚያው ተጉዤ ነበር። አቶ ዳግማዊ፣ የመጀመሪያ ዲግሪውን በኬሚካል ምህንድስና፣ ሁለተኛ ዲግሪውን በኢነርጂ ሲስተምስ ምህንድስና አጠናቆ ዩኒሊቨር ለተባለው ዓለም አቀፍ ኩባኒያ መስራት ከጀመረ አምስተኛ ዓመቱን ይዟል። ቀደም ሲል ለበርካታ ጊዜያት ወደ ደቡብ አፍሪካ የተጓዝኩ ቢሆንም ይህ ጉዞ ከሌሎቹ ጉዞዎቼ የተለየ ነበር። የዚህም ዋነኛው ምክንያት ከ4,500 ኪሎ ሜትር በላይ የሸፈነ የአስራ ሁለት ቀን የመኪና ጉዞን በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከልጄ ጋር ማድረጋችን ነበር። በዚህም፣ አብዛኛውን የደቡብ አፍሪካን መካከላዊ፣ ደቡብ ምስራቃዊ እና ደቡባዊ ግዛቶች ያካለልን ሲሆን በጉዞ መስመራችን ላይ ያሉ ዋና ዋና ከተማዎችን፣ ታሪካዊ ስፍራዎችን እና የቱሪስት መስህቦችን ለመጎብኘት ችለናል። ይህም ሃገሪቱ ያላትን ድንቅ የተፈጥሮ ሃብት እና ማህበራዊ ብዝሃነት በይበልጥ ለመረዳት አስችሎናል።

ይህ ጉዞ በቀን በአማካይ እስከ አራት መቶ ኪሎ ሜትር መንዳት የሚጠይቅ ነበር። ይህን ጉዞ ይበልጥ አስደሳች ያደረገው፣ በየእለቱ በተለያዩ ርእሶች ላይ የምናደርጋቸው ውይይቶች ነበሩ። ሁለታችንም መሃንዲሶች እና በኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ የምንሰራ በመሆናችን ሁሌም የሚያወያዩን ሙያዊ ርእሶች ይኖራሉ። ከሙያዊ ውይይቶች ባሻገር፣ በዚህ ጉዞ ላይ በወቅቱ ያሉትን በርካታ ዓለም አቀፋዊ ፈተናዎችን እና እድሎችን በማንሳት ተወያይተናል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ባለፉት ስልሳ ዓመታት ሐገራችን ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው ውጣ ውረዶች እና በአሁኑ ወቅት ያለችበትን ፈታኝ ሁኔታ አንስተንም ተነጋግረናል። የእነዚህ ውይይቶች ዋነኛ ትኩረት፣ ዛሬ ሐገራችን የምትገኝበትን አስቸጋሪ ሁኔታ እንዴት ልንረዳው ይገባል? ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት ያሉን የመፍትሄ አማራጮች ምንድን ናቸው? እና አሁን ያለው ወጣት ትውልድ ካለፈው ትውልድ ተሞክሮ ምን ሊማር ይችላል? የሚሉ ነበሩ።

በዚህ ውይይት ወቅት በርካታ ነጥቦች የተነሱ ቢሆንም፣ የሚከተሉት ሶስቱ በዋነኝነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ቀዳሚው፣ ለሃገሮች ግንባታ መሰረታዊ የሆነውን እና ባለፉት ስልሳ እና ሰባ ዓመታት የተሸረሸረውን የትውልድ ቅብብሎሽ ማከም አስፈላጊ መሆኑ ነው። ይህንንም ለማሳካት፣ ያለፉት ሶስት እና አራት ትውልዶች ዛሬ ሐገራችን ላለችበት አሳዛኝ እና አሳፋሪ ሁኔታ ያለባቸውን የጋራ ሃላፊነት በማመን ንስሃ መግባት ተገቢ እንደሆነ ተማምነናል። ካለንበት ቀውስ ለመውጣትም እኛ ብቻ አዋቂ ነን ከሚሉ ቁንጽል ልሂቃዊ (Elitist) እና ቡድናዊ

መፍትሄዎች ይልቅ የህዝብ ሉዓላዊነትን አምኖ በተቀበለ መንገድ ሁሉንም የፖለቲካ አመለካከቶች የሚያስተናግድ አሳታፊ እና ፍትሃዊ የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል የሚሉ ናቸው።

በዚህ ጉዞአችን ማጠቃለያ ላይ ልጄ ዳግማዊ አንድ ፈታኝ ጥያቄ አቀረበልኝ። ይኸውም፣ 'ወደእነኚህ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ለመጓዝ አንተ እና የአንተ ትውልድ ምን ልታበረክቱ አስባችኋል?' የሚል ነበር። ይህን ጥያቄ፣ ምንም እንኳን በእኔ ትውልድ ስም የመመለስ ብቃቱ ባይኖረኝም፣ እኔ ያለፍኩበትን ህይወት መለስ ብዬ እንድመረምር እና በምን መልኩ የራሴን ድርሻ ላበረክት እንደምችል እንዳሰላስል አድርጎኛል። ይህም፣ ይህችን አነስተኛ መጽሀፍ ለመጻፍ ዋነኛው እርሾ ሊሆን ችሏል። የመጽሃፉ ዋነኛ መነሻ የእኔ ማንነት ቀዳሚው ትውልድ ባቆየልኝ መሰረት ላይ የተገነባ እንደመሆኑ መጠን ዛሬ ያለውም ትውልድ የእኛው ሥራ እና ጥሪት ውጤት እንደሆነ በጽኑ ማመኔ ነው።

የሐገራችን መጻኢ ዕድል በበጎነት እንዲቀየር ከፈለግን የእኛን ትውልድ የህይወት በጎም ሆነ ስሁት ተሞክሮ በግልጽነት ለተተኪው ትውልድ ማቀበል ተገቢ ይሆናል። በዚህም መሰረት፣ ለዛሬው ትውልድ ሊጠቅሙ ይችላሉ የምላቸውን ተሞክሮዎቼን ከልጅነት፣ ተማሪነት፣ ፖለቲከኛነት፣ መሃንዲስነት እና ዓለም አቀፍ ዲፐሎማትነት ህይወቴ ጋር በማቀናጀት በዚህ መጽሀፍ አቅርቤአለሁ። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ እኔ ከቀደመው ትውልድ የወረስኩትን እና ለማንነቴም መሰረት የሆኑትን እሴቶች በግል የፖለቲካ እና የሙያ ህይወቴ ካካበትኩት ልምድ ጋር በማቀናጀት ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ሞክሬአለሁ። ይህንን በማድረጌም፣ የልጄን እና በእርሱም በኩል የትውልዱን ጥያቄ በመጠኑም ቢሆን በመመለስ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በመጽሃፉ ውስጥ ለሚታዩ ግድፈቶች ሁሉ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

## መግቢያ

የገሃዱን ዓለም ከሚገዙት ምህዳራዊ ህግጋቶች አንዱ እና ዋነኛው የትውልድ ተወራራሽነት (generational succession) ነው። በዚህ ህግ መሰረት፣ ማንኛውም ምህዳር (System) ዘላቂነቱን ሊያረጋግጥ የሚችለው በትውልድ ተወራራሽነት ነው። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው፣ ካለፈው ትውልድ ጠቃሚውን በመውሰድ አዲስ የሚታከለውን በማዳበር ይሆናል። ይህ ሂደት፣ በሁሉም ዓይነት ምህዳሮች ላይ የሚሰራ ቢሆንም በተለያየ የጊዜ ምጣኔ የሚከወን ነው። በመሆኑም፣ በተፈጥሮአዊ ምህዳር ውስጥ የሚኖረው ተወራራሽነት በዋነኝነት ዝግመታዊ (evolutionary) ሲሆን በኢኮኖሚያዊ ምህዳር ውስጥ የሚኖረው ተወራራሽነት በአንጻራዊነት እመርታዊ ይሆናል።

ባለፉት ስልሳ ዓመታት ሐገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የታሪክ መታጠፊያ ተብለው የሚጠቀሱ የለውጥ ወቅቶች እንዳጋጠሟት ይታወቃል። እንዳለመታደል ሆኖ፣ እነኚህን የለውጥ አጋጣሚዎች በአግባቡ ልንጠቀምባቸው ባለመቻላችን ሃገሪቱ ይበልጥ ለተባባሰ የፖለቲካ ቀውስ በመጋለጥ ላይ ትገኛለች። በቅርቡ በሐገራችን የተከሰተው የህዝብ ለህዝብ ግጭት እና ጦርነት ይህ የፖለቲካ ቀውስ የደረሰበትን አስከፊ ደረጃ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ዓቢይ ማረጋገጫ ነው። እንዴት ለዚህ ልንበቃ እንደቻልን መርምሮ መረዳት ወደ መፍትሔው ለማቅናት ዋና መነሻ እንደሚሆን ይታመናል። ለዚህ ደግሞ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተለይም ፖለቲካውን በመዘወር አቢይ ድርሻ ያላቸው ልሂቃን እና ፖለቲከኞች ጥልቅ የሆነ የነፍስያ ፍተሻ (soul-searching) ሊያደርጉ ይገባቸዋል።

ይህን በተመለከተ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተደረጉ ጥቂት ተናጠላዊ ጥረቶች ቢኖሩም፣ አብዛኛው የፖለቲካ ትንተና ለችግሩ ሌሎች ወገኖችን በመውቀስ ራስን ከተጠያቂነት ነፃ ወደ ማውጣቱ ሲያዘነብል ይስተዋላል። እንዲህ ዓይነቱ አመላካከት ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን በተጠያቂነት ከመውቀስ አልፎ አንድን ትውልድ እስከ መርገም ድረስ ደርሷል። ዛሬ ያለችን ኢትዮጵያ፣ እንደ ማንኛቸውም ሃገር፣ በትውልድ ቅብብሎሽ የተገነባች ሃገር ናት። በዚህ ሂደት ውስጥ የነበሩት ትውልዶች እንደየዘመናቸው የራሳቸውን ድርሻ አበርክተው አልፈዋል። የነዚህ ትውልዶች ዋነኛው የውጤታማነት መለኪያቸው ሃገሪቱን ከእነርሱ ዘመን ለተሻለ ሥርዓት ለማብቃት በመቻላቸው ነበር። ይህ እንዲሆን ደግሞ፣ ካለፈው ሥርዓት ጠቃሚውን ማጎልበት እና ዘመኑ የሚጠይቀውን ማከል ይጠይቅ ነበር።

ያለፉት ስልሳ ዓመታት የሐገራችን የፖለቲካ ተራክቦ (discourse) ይህንን መሰረታዊ መርህ የጣሰ በመሆኑ ከድጡ ወደ ማጡ በመግባት ላይ እንገኛለን። በዚህም የተነሳ፣ የስልሳዎቹ ትውልድ የንጉሳዊውን ሥርዓት ትውልዶች በኋላ ቀርነት ሲወቅስ፣ የንጉሳዊው ሥርዓት ትውልዶች እና የደርግ ዘመን ትውልዶች ደግሞ የስልሣዎቹን (ያ ትውልድ) በጥራዝ ነጠቅነት ሲወቅሱ ኖረዋል። ሁሉም ቀዳሚ ትውልዶች ደግሞ አዲሱን የዚህ ዘመን ትውልድ በራስ ወዳድነት እና ሥርዓተ-ቢስነት ሲወቅሱ ይደመጣሉ። ያም ሆኖ፣ በቅርብ ጊዜ ታሪካችን ውስጥ እንደ 1960ዎቹ ትውልድ የተወቀሰም ሆነ የተወደሰ ያለ አይመስለኝም። ዛሬ የምንገኝበት ሃገራዊ ሁኔታ በተጨባጭ የሚያረጋግጠው ሃቅ ሁሉም ተከታታይ ትውልዶች መሰረታዊ በሆነው የትውልድ ሽግግር ፈተና መውደቃችንን ነው።

ለዚህም ነው፣ እያንዳንዱ ቀዳሚ ትውልድ የየራሱን ጥፋት አምኖ ለፈጸማቸው ስህተቶች ንስሃ በመግባት ለተተኪው ትውልድ ሊያስተላልፈው የሚገባውን ጠቃሚ ተሞክሮ ሊያካፍል ይገባዋል የምለው። ይህንንም በማድረግ ዛሬ ካለንበት የትውልድ መርገምት ሽክርክሪት መውጣት እና የተሻለች ሃገር ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ እንችላለን የሚል ተስፋ አለኝ። በዚህ መሰረት፣ በቀዳሚነት እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ በነበረኝ ህይወት ውስጥ በማናቸውም ወቅት ማድረግ የሚገባኝን ባለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባኝን በማድረግ ለፈፀምኳቸው ስህተቶች የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ እወዳለሁ። በማስከተልም፣ ይህንን መጽሀፍ ተተኪው ትውልድ የንስሐዬ መገለጫ አድርጎ እንዲወስድልኝ እጠይቃለሁ።

የዚህ መጽሀፍ የመጀመሪያ ክፍል የወላጆቼን ታሪክ በወፍ በረር በመቃኘት እኔነቴን የቀረጹትን ዋና ዋና ቤተሰባዊ እሴቶች ይዳስሳል። ሁለተኛው ክፍል የተማሪነት ዘመኔን እና ከእርሱ ጋር የተያያዙ ማህበራዊ እሴቶች የሚዳስስ ሲሆን፤ ከዚህ በማስከተል የነበረኝ የፖለቲካ እና የዩኒቨርሲቲ ህይወት ከተያያዥ ውርስ እሴቶቹ ጋር በሶስተኛው እና በአራተኛው ክፍል ተዳሷል። በመቀጠልም፣ አምስተኛው እና ስድስተኛው ክፍል የሥራ እና ዓለም አቀፍ ዲፕሎማትነት ህይወቴን ይዳስሳል። በመጨረሻም፣ በመጽሃፉ ውስጥ በተጠቀሡት ውርስ እሴቶች እና የግል ተሞክሮዎች ላይ በመመርኮዝ ለሐገራችን የፖለቲካ ህመም የፈውስ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ የምላቸው ሃሳቦች በሰባተኛው ክፍል ቀርበዋል። መጽሃፉ በሶስት ሺህ ኮፒ ታትሞ በዛጎል የመጽሃፍ ባንክ እና ሌሎች ተቋማት በኩል በነጻ በመሰራጨት ላይ ይገኛል። ሰፋ ላለ ስርጭት እና ውይይት እንዲያመች በማሰብ የመጽሃፉ ሰባተኛ ምዕራፍ በዚህ መልክ ተዘጋጅቷል።

*መልካም ንባብ እና ውይይት*

## 7. የትውልድ ውርስ እና ሃገር

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው እኔ በተለምዶ 'ያ ትውልድ' ተብሎ የሚታወቀው ትውልድ አካል ነኝ። በመሆኔም የ1966ቱ የህዝብ እንቅስቃሴ ካስከተለው የመንግሥት ለውጥ አንስቶ ሶስት ከፍተኛ የመንግሥት ለውጥን ለማየት ችያለሁ። ከእነዚህ ለውጦች ውስጥ በመጀመሪያው ለውጥ ወቅት ንቁ ተሳታፊ ነበርኩ ማለት ይቻላል። በዚህም፣ ውድ ከሆነው የወጣትነት ዘመኔ ውስጥ አስር ዓመታትን በንቁ ፖለቲከኝነት እና እስረኝነት አሳልፌአለሁ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ከእድሜዬ በላይ ከቀበሌ እስከ ክፍለ ሃገር የዘለቀ የፖለቲካ ሃላፊነት መያዝ በመቻሌ በርካታ የህይወት ልምዶችን እና አስተዳደራዊ ዕውቀቶችን ማግኘት ችዬ ነበር። ይህ በኋላኛው የህይወት ዘመኔ ካካበትኩት ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ጋር ተዳምሮ የማንኛውንም ሃገር ፖለቲካዊ መስተጋብር ለመረዳት የሚያስችል ክህሎት ማዳበር ችዬአለሁ ማለት ይቻላል።

ከእነኚህ ዓመታት ያገኘሁት ትምህርት ምንም እንኳን ጥቂቶች በፍጹም ቀናነት ለህዝብ መሰረታዊ መብት እና ጥቅም የሚቆሙ ቢኖሩም፣ በጌታ እና ሎሌ መንፈስ ከተለወሰው ፖለቲካዊ ውርሳችን የተነሳ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ መሪዎች ከምንም በላይ ለጠባብ የግል እና ቡድን ጥቅም የሚሰሩ መሆናቸውን ነው። ይህም በመሆኑ፣ ከመጨረሻው እስር በተፈታሁበት ወቅት በቀሪው ዘመኔ በሚኖረኝ የትምህርትም ሆነ የሥራ ተሳትፎዬ ከፖለቲካ ለመራቅ ወሰንኩኝ። በዚህ መሰረት ከ1975 አንስቶ ስለሃገር በሚደረጉ የተናጠል ውይይቶች ሃሳብ ከመስጠት ያለፈ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ተሳትፎ አልነበረኝም። ያም ሆኖ፣ ለውጦች በመጡ ቁጥር ሰሚ ሊገኝ ይችላል በሚል ተስፋ ለአዲስ መጪዎቹ መሪዎች ሃሳቤን ከማካፈል አልተቆጠብኩም።

በዚሁ መሰረት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ኢህአዲግ ስልጣን እንደጨበጠ በአንድ የድርጅቱ ከፍተኛ መሪ በኩል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ያልኩትን ሃሳቦች ለማካፈል ሞክሬአለሁ። ይህ ሙከራ ግን ከወራቶች የዘለለ አልነበረም። የ2010ን የህዝብ እንቅስቃሴ ተከትሎ የመጣው የመንግሥት ለውጥ እንደማናቸውም የለውጥ ወቅቶች በርካታ ተስፋዎችን ይዞ የመጣ ነበር። ይህ ወቅት እኔም በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ የነበረኝን ሃላፊነት ለቅቄ ወደ ሃገሬ የተመለስኩበት ወቅት በመሆኑ ሂደቱን በቅርብ ለመከታተል አስችሎኛል። ባለፉት አምስት ዓመታት፣ ምንም እንኳን አንዳንድ ወገኖች በተለያየ ወቅት ወደ ፖለቲካ እንድገባ ሙከራ ቢያደርጉም በቀደመው ውሳኔዬ በመጽናት ንቁ ተሳታፊነትን ስከላከል ቆይቻለሁ። ይህ ውሳኔዬ በቀሪ ዘመኔም የሚቀየር አይሆንም።

የዚህ ውሳኔ ዋነኛው ምክንያት ለፖለቲከኝነት የሚያበቃ ግለ-ባህሪ የለኝም ብዬ ማመኔ ሲሆን በሁለተኝነት ከሰላሳ ዓመታት በላይ ከተሰማራሁበት ሙያ ጋር በተያያዘ ለአጠቃላይ የሰው ልጆች አካባቢያዊ ደህንነት እና ዘላቂ ልማት የሚጠቅም አነስተኛ አስተዋጽኦ እያደረኩ መሆኑን በማመኔ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሐገራችንን የወደፊት እጣ ፈንታ በሚመለከት በማናቸውም ወቅት በዕውቀት ላይ የተመረኮዘ ግብዓት ከመስጠት ወደኋላ አላልኩም፣ ወደፊትም አልልም። እኔ ራሴን ከፖለቲካው ማግለሌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ውጥንቅጡ በወጣ የፖለቲካ ሜዳ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ለሚጥሩ የሙሉ ጊዜ ፖለቲከኞች አድናቆት አለኝ። ባለፉት ዓመታት በሐገራችን ኢትዮጵያ ለተፈጠሩት የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ተጠያቂ የማደርገው በየትኛውም ዘመን የነበሩ ፖለቲከኞችን ሳይሆን ሲንከባለል የመጣውን የፖለቲካ ባህል ውርሳችንን ነው። መፍትሄውም እርስ በርስ መወነጃጀል ሳይሆን የችግሩን ምንጭ ለይቶ መፍትሄ መሻት ነው። በዚህ ምዕራፍ የተካተቱት ሃሳቦች በዚህ መንገድ ለሚካሄዱ ጥረቶች መጠነኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ የሚል እምነት አለኝ።

## 7.1 የምህዳራዊ አስተሳሰብ አስፈላጊነት

የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች ከቀደመው ዘመን ፈተናዎች እጅግ የተወሳሰቡ መሆናቸው ሁለንተናዊ ተቀባይነት ያገኘ ዕውነታ ነው። በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘርፍ አየታየ ያለው እጅግ ፈጣን እድገት ዛሬ ያሉትን ዓለም አቀፋዊ ፈተናዎች ይበልጥ ውስብስብ እያደረጋቸው እንደሚሄድም ይጠበቃል። ሐገራችን ኢትዮጵያም የእነዚህ ውስብስብ ፈተናዎች ተጋሪ መሆኗ አያጠራጥርም። ይህንን ለመረዳት፣ ለማህበራዊ ሚዲያዎች መስፋፋት የተፈጠረው አመቺ ሁኔታ የህዝቦችን ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማጎልበት የጠቀመውን ያህል በህዝቦች መሃል ግጭቶችን ለማስፋፋት እና አምባገነን ሥርዓቶችን ለማጠናከር የዋለበትን ሁኔታ መመልከቱ በቂ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ ፈጣን እድገት እያሳየ የመጣው የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) ቴክኖሎጂ ተጨማሪ ውስብስብነቶችን እንደሚያመጣ ይጠበቃል። እነኚህን ፈተናዎች ለመሻገር ያሉትን ችግሮች በተናጠል መረዳት እና አቅላይ (simplistic) መፍትሄ መስጠት ሳይሆን ውስብስብነታቸውን ተገንዝቦ በሁለንተናዊ (holistic) አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ መፍትሄ መሻት ያስፈልጋል።

ዛሬ ባለንበት ሁኔታ የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ዋነኛው መሰረቱ ደግሞ የውስብስብነት ሳይንስ ተብሎ የሚታወቀው ምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ከሐምሌ 2012 ዓም አንስቶ ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ የሐገራችንን የፖለቲካ ምስቅልቅል ሊፈቱ ይችላሉ ያልኳቸውን

ሃሳቦች በተለያዩ ሚዲያዎች ለማካፈል ሞክሬአለሁ። እነኚህን ሃሳቦች በይበልጥ በማበልጸግም በየካቲት 2013 ዓም 'ምህዳራዊ አስተሳሰብ፡ ለዘላቂ ሐገራዊ መፍትሔ' የሚል መጽሀፍ በማሳተም ለሚመለከታቸው ወገኖች እና አንባቢዎች በነጻ እንዲዳረስ አድርጌአለሁ። ይህንኑ ጥረት እስከ ነሐሴ 2013 በመቀጠልም በተለያዩ የሐገራችን ፈተናዎች እና ጉዳዮች ላይ ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ተሞክሯል። በመጨረሻም፣ በየካቲት 2014 ዓም የሐገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን መመስረት ተከትሎ፣ ለሐገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት ይበጃሉ ያልኳቸውን ሃሳቦች በቀጥታ ለኮሚሽኑ አካፍያለሁ።

በእነኚህ መጣጥፎች ላይ የሀገራችንን የወቅቱን ፈተናዎች ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ ለመርመር እና ወደ መፍትሄው ሊወስዱ ይችላሉ ያልኳቸውን ሃሳቦች ለማካፈል ተሞክሯል። ለአንባቢዎች መጠነኛ ግንዛቤ ለመስጠት ያህል፣ በእነኚህ አበርክቶዎቼ አበክሬ ለማስገንዘብ ከሞከርኳቸው ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

i. ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ፈተናዎች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት የችግሩን ውስብስብነት ጠንቅቆ መረዳት እና ለተጨማሪ ውስብስብነት ከሚዳርጉ ቁንጽል እና አቅላይ (የጥቁር ወይም ነጭ) መፍትሔዎች መቆጠብ ያስፈልጋል።

ii. ለዚህም እንዲረዳ የትኛውም የፖለቲካ ቡድን የራሱን 'እውነት' በሌሎች ላይ በሃይል ለመጫን ከመሞከር ተቆጥቦ የሌሎች ማህበረሰብ ክፍሎችን እና ፖለቲካ ቡድኖችን 'እውነት' ለማድመጥ እና 'የጋራ እውነታን' ለመፍጠር መጣር ይኖርበታል።

iii. ይህ እውን እንዲሆን የፖለቲካ ልሂቃኖቻችን ከመናገር በበለጠ በእጅጉ የሚጎላቸውን እና በብዙ ማህበረሰቦቻችን በሰፊው የሚገኘውን ሌሎችን ከልብ የመስማት እና የማድመጥ ባህልን ማዳበር እና ከፉክክር በበለጠ ትብብርን እንደ ዋነኛ የአደረጃጀት መርህ ሊከተሉ ይገባል።

iv. በኢትዮጵያዊነታችን ሊያኮሩን እና ሊያሰተሳስሩን የሚችሉ የታሪክ ድርሳኖች የመኖራቸውን ያህል ልናፍርባቸው እና ይቅር ልንባባልባቸው የሚገባን የታሪክ ምዕራፎች እንዳሉን አምነን መቀበል እና ከነኚህም ለመማር ዝግጁ መሆን ይኖርብናል።

v. ሐገራችን ኢትዮጵያ በዘመናት ቅብብሎሽ ውስጥ ለተለያዩ የማንነት ቀውሶች የተዳረጉ በርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚገኙባት ሃገር መሆኗን መረዳት እና ይህንን ለማከም የሚወሰዱ እርምጃዎችም አዳዲስ የማንነት ቀውሶች እንዳይፈጥሩ መከላከል ያስፈልጋል።

vi. ከታሪካዊ ውርሶቻችን አኳያ የግለሰብን መብት ከማክበር ባልተናነሰ መልኩ የቡድን መብቶችን ማስከበሩ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት እና የግለሰብ እና የቡድን መብቶችን በተወራራሽነት ሳይሆን በተደጋጋፊነት ለማክበር የሚያስችል መንግሥታዊ ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል።
vii. ከሐገራዊ እውነታ እና ከተጨባጭ የህዝብ ፍላጎት ጋር የማይጣጣሙ የፖለቲካ አስተሳሰቦች እና የማህበረሰብ እድገት ሞዴሎችን ከውጭ ገልብጦ በጅምላ እና በጭፍን ለመተግበር መሞከር ለተጨማሪ ሃገራዊ ምስቅልቅሎች እንዳይዳርገን መጠንቀቅ ይገባናል።
viii. በኢትዮጵያ የሐገረ መንግሥት ምስረታ ታሪክ ውስጥ ያሉትን መዋቅራዊ ችግሮች ጠንቅቆ መረዳት እና በአፈታታቸው ላይ ሐገራዊ መግባባትን መፍጠር ለዘላቂ መፍትሔ ዋነኛው መሰረት ነው። ይህ ሂደትም የህዝብን ሉዓላዊነት በሚያከብር መልኩ መከናወን አለበት።
ix. በአሁኑ ወቅት በፖለቲካ ልሂቃኖቻችን የሚራመዱ ተቃራኒ (conflicting) ተረኮችን ወደ ዓይነታዊ የለውጥ ተረኮች (transformational) ማሸጋገር የሐገራዊ ምክክሩ ዋነኛው ትኩረት ሊሆን ይገባዋል።
x. ይህንን ሁሉ ለማሳካት በሰፊው ከሚታየው እና በተቀነበበ ትንተና (reductionist) ላይ ከተመረኮዘው ፖለቲካዊ አስተሳሰባችን በምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) ወደተቃኘ አእምሮአዊ ውቅር መሸጋገር ያስፈልገናል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እና ቀደም ሲል በተሰራጩት ጽሁፎች ውስጥ የቀረቡትን ሃሳቦች ለመረዳት እና ተግባራዊ ለማድረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ በተወራረሰው ፖለቲካዊ ባህላችን የተቃኘውን አእምሮአዊ ውቅራችንን በጥልቅ መፈተሽ ይኖርብናል። ይህንንም በማድረግ እስካሁን ለመጣንበት እና አሁንም ላለንበት የፖለቲካ ምስቅልቅል የዳረጉንን አንካሳ የትውልድ ውርሶቻችንን አስወግደን ለዘመኑ የሚመጥን ፖለቲካ ወደ ማራመዱ ልንሸጋገር እንችላለን። ይህንን በማድረጉ ረገድ የነገይቱ ኢትዮጵያ ባለቤት የሆነው እና በብልሹው የፖለቲካ ባህላችን ሙሉ ለሙሉ ያልተተበተበው ወጣቱ ትውልድ ከፍተኛ ሀገራዊ ድርሻ ይኖርበታል።

## 7.2 የአዕምሮአዊ ውቅር ለውጥ

ሐገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ስልሳ ዓመታት የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ህይወት ለቀጠፉ ተከታታይ የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ተዳርጋለች። ባለፉት አምስት ዓመታት ይህ ፈተና ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ከፖለቲካ ተዋንያኖቹ አልፎ ሴቶች እና ህጻናትን ጨምሮ ለበርካታ ሰላማዊ ዜጎች ህይወት መጥፋት እና መፈናቀል ምክንያት መሆኑ እጅግ ልብ ይሰብራል። በተለይም፣ በሃገሪቱ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሰሜኑ የሐገራችን ክፍል የታየው የሕዝብ ለሕዝብ እልቂት በታሪካችን ላይ አሳፋሪ ጥቁር ጠባሳ ከመተዉም በላይ ለትውልድ የሚሸጋገሩ ፈተናዎችን ትቶልን አልፏል። ለዚህ አሳፋሪ ታሪክ አስተዋጽኦ ያደረጉ የፖለቲካ መሪዎች በግንባር ቀደምትነት የተጠያቂነት ድርሻ ቢኖራቸውም ሁላችንም እንደ ማህበረሰብ የወደቅንበት በመሆኑ የጋራ ሃላፊነት ልንወስድ ይገባል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በአሁኑ ወቅት ያለው የሐገራችን የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ሁኔታ በአንዳንድ ዓለም አቀፍ የጥናት ሰነዶች እንደተመለከተው የሃገሪቱ ቀጣይ ህልውናን ጥያቄ ውስጥ የማስገባት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዘመናት ለሐገራችን ህዝቦች መተሳሰር እና መተሳሰብ ዋነኛ መሰረቶች በሆኑት ተቋማት ላይ ከሚደረገው ዘመቻ ጋር ተቀናጅቶ ሲታይ እጅግ አሳሳቢ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ሃገሪቱን ለማንኛችንም በማትሆን መልኩ በላያችን ላይ እንድትፈርስ (implode) የሚያደርጋት መሆኑን ሁሉም ወገኖች ሊረዱት ይገባል። ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በዘላቂነት ለመውጣት አጠቃላይ የፖለቲካ ባህላችንን እና አስተሳሰባችን መፈተሽ እና መሰረታዊ ህመሙን ማከም ያስፈልጋል።

በእኔ እምነት፣ እየተባባሰ የመጣው የሀገራችን የፖለቲካ ምስቅልቅል ሲወራረስ ከመጣው የሀገረ መንግሥት ምስረታ እና ከዚያም ጋር ተያይዞ ከወረስነው የፖለቲካ ባህላችን ጋር የተያያዘ ነው። ይህንንም ለማከም የሚጠቅመው ለእያንዳንዱ ዘመን ችግሮቻችን ተጠያቂዎችን መፈለግ ሳይሆን የዚህ ሁሉ መሰረት የሆነውን አእምሮአዊ ውቅራችንን (mental model) መፈተሽ ነው። ዛሬ ያለውን የፖለቲካችንን መሰረታዊ ባህርይ በዋነኝነት እየቀረጸ ያለው ከተከታታይ ትውልዶች በወረስነው የፖለቲካ አስተሳሰብ እና ልማድ የተቃኘው አእምሮአዊ ውቅራችን ነው። ባላፉት ስልሳ ዓመታት የተራመዱት የፖለቲካ አስተሳሰቦች 'ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ' በሚያስብል መልኩ የዚህ ችግር ሰለባዎች ናቸው። በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የሚታየው ምስቅልቅልቅ ተስፋ አስቆራጭ ቢሆንም፣ ወጣቱን ትውልድ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መሰረታዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ችግሮች ማንጻት ከተቻለ የወደፊት እጣ ፈንታችንን መቀየር ይቻላል የሚል ዕምነት አለኝ።

### *7.2.1 ባላባታዊ አስተሳሰብ*

*ተደጋግሞ እንደተነገረው ሀገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ምዕተ ዓመታቶች የሃገረ መንግሥት ታሪክ ካላቸው ጥቂት ሃገሮች አንዷ ናት። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ይህ የሃገረ መንግሥት ታሪካችን ወጥ በሆነ መልኩ በጥቂት መሳፍንታዊ ቤተሰቦች መካከል በሚካሄድ ባላባታዊ የሥልጣን ፉክክር ላይ የተመረኮዘ ነበር። የዚህም ዋነኛው መገለጫዎች በዋናዎቹ ተፎካካሪ ሃይሎች መካከል የሚካሄድ የሴራ ትንንቅ እና ለበርካታ ህዝብ እልቂት ምክንያት የሆኑ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ነበሩ። የሀገረ መንግሥት ማዕከሉም ይህንኑ የሃይል ሚዛን ተከትሎ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ሲዋልል ኖሯል። በእነኚህ የመንደር እና ጎሳ መሳፍንቶች መካከል በተካሄደው ግብግብ ውስጥ አብዛኛው የሐገራችን ህዝብ የመከራው ገፈት ቀማሽ ሆኖ ቆይቷል።*

*ይህ የፖለቲካ ህመም ባላፉት ሃምሳ ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠሩ እና አሁንም ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥም ጎልቶ ታይቷል። ይኸው 'እኛ እናውቅልሃለን' በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘው ባላባታዊ ፖለቲካ በአንድ ድርጅት የፖለቲካ ህይወት ውስጥ የጥቂቶች አዛዥ ናዛዥነት እና የብዙሃኑ የፖለቲካ ጭሰኝነት ገኖ የሚታይበት ሁኔታ ፈጥሯል። በመሆኑም፣ በ1966 ለውጥ መጀመሪያ ላይ ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎባቸው በነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እንኳን ጥቂቶች ባላባት የሆኑበት እና አብዛኛው የፖለቲካ ጭሰኛ የተደረገበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። በዚህም ምክንያት ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የ1960ዎቹ የወጣቱ እንቅስቃሴ እና መስዋእትነት ሁሉ እንዳልነበር ሁኗል። እስካሁን በቀጠለው በዚህ ህመማችን የተነሳ የሐገራችን ፖለቲካ ከዕለት ወደ ዕለት ከድጡ ወደ ማጡ እየዘቀጠ በመሄድ ላይ ይገኛል።*

*ወጣቱ ትውልድ ይህንን የበሽታችንን ዋነኛ ምንጭ ጠንቅቆ በመረዳት ራሱንም ሆነ በዙሪያው የሚገኙትን የፖለቲካ መሪዎች ከዚህ የባላባታዊነት ፖለቲካ አስተሳሰብ በማንጻት የራሱን እና የሃገሩን መጻኢ ዕድል መቀየር ይገባዋል። የዚህም ዋነኛው መገለጫ ከመሪዎቹ የሚንቆረቆሩለትን ሃሳቦች ለዘመኑ በሚመጥን እውቀት እና ሃገራዊ ዕውነታ ላይ ተመርኩዞ መሞገት እና የብዙሃኑን የሃሳብ ልዕልና ማረጋገጥ ይሆናል። ከቀደመው ታሪካችን እና ሃገር በቀል ዕውቀቶቻችን ልንወስድ የምንችላቸው ጠቃሚ ትምህርቶች ቢኖሩም የሃያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን ፈተናዎች በአስራ ዘጠነኛው ወይም በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰቦች መሻገር እንደማይቻልም መረዳት ተገቢ ይሆናል።*

### *7.2.2 የግለ-አምልኮ ፖለቲካ*

ከባላባታዊ አስተሳሰባችን በጥብቅ የሚተሳሰረው ሌላው የፖለቲካ ህመማችን በፖለቲካ ባህላችን ውስጥ ገኖ የሚታየው የግለ-አምልኮ ፖለቲካ (cult-politics) ነው። ይህም የሚያያዘው ለዘመናት የነበሩት ተከታታይ ንጉሣዊ ሥርዓቶች የአገዛዛቸውን ቅቡልነት በህዝቡ ላይ ለማስፈን ይጠቀሙበት ከነበረው ዋነኛው መንገድ በሰማያዊው አምላክ የተቀቡ መሆናቸውን ማስነገር እና ማሳመን ከመሆኑ ጋር ነው። ለዚህም በህብረተሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያላቸውን የሃይማኖት እና የእምነት ተቋማትን በዋነኝነት ሲጠቀሙባቸው ኖረዋል። በዚህም የተነሳ፣ ንጉሣዊያኑ ራሳቸውን ‘ሥዩመ-እግዚአብሔር’ ብለው እስከመሰየም ከመድረሳቸውም ባሻገር አብዛኛው የህበረተሰብ ክፍልም ይህንኑ ተቀብሎ መሪዎቹን አይተኬነት እና መለኮታዊነት ሲያላብስ ኖሯል።

ይህ የተሳሳተ አመለካከት እጅግ ስር የሰደደ በመሆኑ የተነሳ በተለያየ ወቅት የሃገሪቱ ቀጣይነትም በወቅቱ ከነበሩት መሪዎች በህይወት መቆየት ጋር በማያያዝ ለመሪዎች ረዥም እድሜ ስንለምን ኖረናል። በቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንኳን አብዛኛው ህዝብ የሀገሪቱን ህልውና ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኋላም ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም እና ከአቶ መለስ ዜናዊ በሥልጣን መቆየት ጋር ሲያይዝ ኖሯል። ነገር ግን ሁሉም አልፈው የሃገሪቱ ህልውና እስካሁን ድረስ ዘልቋል። ይህ አምልኮአዊ እምነት ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ ዛሬ ላይ ቆመውም የቀደሙትን መንግሥታቶች ‘መልካም ጊዜ’ እያሰቡ የሚቆዝሙ ብዙ ናቸው። እንዲህ አይነቱ አምልኮ በሃገር ላይ ከሚያስከትለው ጥፋት ባሻገር ራሳቸው መሪዎቹንም መጀመሪያው ላይ ከነበራቸው ቀና አመለካከት ፍጹም ወደሆነ አምባገነንነት እንዲቀየሩ ሲገፋቸው ተመልከተናል። ለዚህም፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ጊዜ ከነበራቸው ተራማጅነት ወደ ፍጹማዊ ንጉሥነት የተሸጋገሩበትን ሂደት እና በተከታታይ መሪዎች ላይ የተስተዋለውን መሰል የግለ-አምልኮ ሽግግር መጥቀስ ይቻላል።

የሚያሳዝነው ነገር ይህ ለዘመናት ስር ሰዶ የኖረ የሥነ መንግሥት አስተሳሰስብ በዘመናዊ ፖለቲካችንም ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ይዞ መዝለቁ ነው። በመሆኑም፣ ይኸው የግለ-ዓምልኮ አስተሳሰብ በመንግሥታቶቻችን ላይ ብቻ ሳይሆን የፓርቲ ፖለቲካ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በፖለቲካ ፓርቲዎቻችንም ውስጥ ገኖ የሚታይ ግልገል በሽታ ለመሆኑ በርካታ ማሳያዎች ማቅረብ ይቻላል። ወደኋላ መለስ ብለን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሜዳ የነበሩትን እና አሁንም ያሉትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ ስንመለከት አነሳሳቸውም ሆነ ወድቀታቸው የሚያያዘው ከዚሁ የግለ-ዓምልኮ ፖለቲካ መስፈን እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ከሚፈጠር የውስጥ

ቡድን ሽኩቻ እና መፈረካከስ ጋር መሆኑን እንረዳለን። በጥቅሉ፣ የግለ-ዓምልኮ ፖለቲካ ሃገር አጥፊ ብቻ ሳይሆን ራሱ ተመላኪ የሆነውን የፖለቲካ መሪም የሚበላ በመሆኑ ወጣቱ ትውልድ ከእንዲህ አይነቱ አመለካከት ራሱን ማንጻት እና መሪዎቹንም ወደ እዚህ ወድቀት ከመግፋት መቆጠብ ይኖርበታል።

### *7.2.3 ወለፈንዲ ፌደራሊዝም*

የፌደራሊዝም ዋነኛ ግቡ የግለሰቦችን መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና የሕዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሚያስከብር ያልተማከለ የሕዝብ አስተዳደር መመስረት ነው። ታሪካችንን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፣ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ የዘለቀውን የአካባቢ ንጉሦች ለአንድ ንጉሠ ነገሥት የሚገብሩበት ሥርዓት ያልተማከለ አስተዳደር የሚለውን የፌደራሊዝም መርህ በግርድፉ የሚከተል ይመስላል። ሆኖም ግን የግለሰቦች ሰብዓዊ መብቶች እና የህዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶችን የሚደፈጥጥ በመሆኑ ሃገሪቱን ለተከታታይ የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ዳርጓታል። በዚህ ረገድ፣ ጠያቂ የህብረተሰብ ክፍል በተፈጠረበት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ዘመን የግለሰቦች እና የህዝቦች መብት መደፍጠጥ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት እና ንጉሠ ነገሥታዊ ሥርዓቱም ወደ ፍጹም አሃዳዊነት የተሸጋገረበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። የየካቲት ስልሳ ስድስቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የዚህ ነባራዊ እውነታ አይቀሬ ውጤት ነበር።

የንጉሠ ነገሥቱን ከስልጣን መወገድ ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጣው ወታደራዊ መንግሥት ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን ላዋለዱ የሕዝብ መሰረታዊ የመብት እና አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠት ይልቅ የወረሰውን ፍጹም አሃዳዊ ሥርዓት በሶሻሊስታዊ አስተሳሰብ ሽፋን ለማስቀጠል በመሞከሩ ለወድቀት ተዳርጓል። ወታደራዊ አገዛዙን ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጣው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዲግ) ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ የፌደራሊዝም መርሆዎች በሶሻሊስታዊ ቃና ቃኝቶ ለመተግበር ሞክሯል። ነገር ግን ይህ ሙከራ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ዋነኛ የፖለቲካ ህመሞች የጸዳ ባለመሆኑ፣ የዜጎች መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች በቡድን መብቶች እንዲጨፈለቁ ከማድረጉም በላይ እጅግ የተማከለ የፌደራል እና የክልል መንግሥታትን ሊፈጥር በቅቷል። በዚህም የተነሳ ዛሬ ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ከነበረችው የዘመነ መሳፍንቷ ኢትዮጵያ ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ ሃገሪቱ በእርስ በእርስ ግጭት እና ጦርነቶች የምትታመስ ሆናለች።

በአሁኑ ወቅት ሐገራችን ከምትገኝበት የፖለቲካ ምስቅልቅል ለመውጣት ከፌደራላዊ የአስተዳደር መዋቅር የተሻለ አማራጭ እንደሌለ የንጉሣዊ ሥርዓቱን መመለስ ከሚያልሙ ወገኖች በስተቀር አብዛኛው የፖለቲካ ልሂቃን ያምናል። ልዩነቱ ያለው ምን ዓይነት ፌደራላዊ ሥርዓት የሚለው ላይ ነው። በዚህ ረገድ ዛሬ ያለውን የግለሰቦችን መብት ለቡድን መብት ተገዢ የሚያደርግ ሥርዓት እንዳለ ማስቀጠልም ሆነ የቡድኖችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ወደጎን አድርጎ በዜጎች መብት ላይ ብቻ የተመረኮዘ ሥርዓት ለመፍጠር ማሰብ ሊተገበር የማይችል (unviable) መፍትሄ ከመሆኑም በላይ አንዱን ወይም ሌላውን የፌደራሊዝም መርህ የሚጥስ ነው።

ከዚህ ይልቅ፣ የወጣቱ ትውልድ ትኩረት መሆን ያለበት በቀዳሚነት የሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ሰዓት ያለው ፌደራላዊ ሥርዓት በየትኛውም ክልል የሚገኙ ዜጎችን መሰረታዊ የሆኑ በህይወት የመኖር፣ የመስራት፣ ሃብት የማፍራት እና በአካባቢያዊ አስተዳደር የመሳተፍ መብታቸው እንዲከበርላቸው ማድረግ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን፣ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ በፌደራል እና በክልል መንግሥታት ደረጃ ተማክሎ የሚገኘውን መንግሥታዊ አስተዳደር ባልተማከለ እና ለእውነተኛ የሕዝብ ተሳታፊነት እና ተደራሽነት ምቹ በሚሆኑ የአስተዳደር መዋቅሮች መተካት ይሆናል[1]። ይህንንም በማድረግ መሰረታዊ መርሆዎቹን የጠበቀ የፌደራል ሥርዓት ከመገንባትም በላይ ዛሬ ከየቅጣጫው ለሚነሱ ራስን በራስ የማስተዳደር (ለምሳሌ የጉራጌ እና ወላይታ) ጥያቄዎችም ተገቢ ምላሽ መስጠት ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ከመቼውም በበለጠ ለሃገር ህልውና ስጋት እየሆነ የመጣውን የሶስቱን (አማራ፣ ኦሮሚያ እና ትግራይ) ክልሎች ልሂቃን መገፋፋትንም ሊቀንሰው ይችላል።

### *7.2.4 ኢሕገመንግሥታዊ ህጋዊነት*

ከላይ የተጠቀሰው ርዕስ እርስ በእርሱ የሚጋጭ (oxymoron) መስሎ ሊታይ ይችላል። ነገር ግን በሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የታዩትን እና ራሳቸውን ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ብለው የሰየሙ መንግሥታቶችን በትክክል የሚገልጽ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በመሰረቱ፣ ሕገመንግሥት የአንድ ሃገር ህዝብ እንደ ህዝብ ከተጎናጸፈው መብቶች ቀንሶ እና ለክቶ ለመንግሥት የሚሰጥበት እና ይህም በአግባቡ መተግበሩን የሚቆጣጠርበትን ሥርዓት የሚደነግግበት ሰነድ ነው። ነገር ግን ከቀዳሚው የሐገራችን ሕገመንግሥት ብንጀምር፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ

[1] በዚህ ረገድ የስዊትዘርላንዱን የካንቶን አደረጃጀት ሥርዓት እና የናይጄሪያን የፌደራል አደረጃጀት ልምዶች መመርመሩ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

*ሕገመንግሥት ንጉሠ ነገሥቱ በ’መልካም ፈቃዳቸው’ የሰጡን እና የራሳቸውን ፍጹማዊ የዘውድ አገዛዝ ያሰፈኑበት እንደነበር ይታወቃል። ያንን ተከትሎ የመጣው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (አሕዲሪ) ሕገመንግሥት በሶሻሊስታዊ ካባ ተሸፍኖ የአንድን ግለሰብ እና ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለማስፈን በፓርቲው ተለክቶ የተሰፋ ሕገመንግሥት በመሆኑ የህዝብ ቅቡልነት ሳያገኝ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈረካከስ ችሏል።*

*የ1983ቱን ለውጥ ተከትሎ የመጣው እና ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሰረት የሆነው ሕገመንግሥት በአብዛኛው የፌደራሊዝም መሰረታዊ መርሆዎችን የተከተለ መምሰል ብቻ ሳይሆን በርካታ የዲሞክራሲያዊ ፌደራሊዝም ዝርዝር መርሆዎችን የያዘ በመሆኑ ከቀደሙት የተሻለ ነበር። ነገር ግን፣ ከዚህ አለፍ ብሎ በወቅቱ የበላይነት የነበረውን ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም መርሆዎች በውስጡ በማካተቱ እንደማንኛውም የፓርቲ ሰነድ ራሱን ለትችት እና ወቀሳ አጋልጧል። ከዚህም በላይ፣ እነዚህ በሕገመንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ የፖለቲካ ፓርቲ እምነቶች በየክልሉ የተለያየ ትርጓሜ በመያዛቸው በሕገመንግሥቱ ውስጥ የተካተቱትን መሰረታዊ የዜጎች መብት እንዲደፈጠጥ ከማድረጋቸውም በላይ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ በተቃርኖ የተሞላ እና ቅቡልነት የሌለው እንዲሆን አድርጎታል። ይህም በየደረጃው ተበራክቶ ለሚታየው ኢሕገመንግሥታዊ ህጋዊነት መነሻ ሊሆን ችሏል።*

*ከዚህ ችግር ውስጥ ለመውጣት የምንከተለው መንገድ አሁን በስራ ላይ ያለውን እና በርካታ ጠቃሚ ድንጋጌዎች ያለውን ሕገመንግሥት ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማ ማስፈጸሚያ የሆኑትን አንቀጾች ለይቶ በማውጣት የህዝብ ቅቡልነት ያለው ሕገመንግሥት የማሻሻል ስራን መስራት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በቀዳሚነት በፌደራል እና ክልላዊ ሕገመንግሥቶች መካከል ያሉ የይዘት ተቃርኖዎችን ‘የፌደራሉ ሕገመንግሥት የሃገሪቱ ገዢ ህግ ነው’ በሚለው መርህ መሰረት ማስወገድ ያስፈልጋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ፣ በፌደራሉ ሕገመንግሥት ውስጥ ከተደነገጉት የዜጎች መብት ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ ክልሎችን እና በክልሎች ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶችን የአንድ ብሔረሰብ አድርገው የሚደነግጉ የክልል ሕገመንግሥታት ድንጋጌዎች እና ከዚያም የሚመነጩ ህጎች እና ደንቦች ናቸው።*

*ከዚህ በላይ የቀረበው የመፍትሄ ሃሳብ፣ ‘ይህ ሕገመንግሥት የሚነካው በመቃብራችን ላይ ነው’ የሚሉትንም ሆነ ‘የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ በስራ ላይ ያለው ሕገመንግሥት ስለሆነ መወገድ አለበት’ የሚሉትን ወገኖች እንደማያስደስት እገምታለሁ። እነኚህን ወገኖች የማሳስበው ሁለቱም ጽንፍ ላይ ያሉ አቋሞች ወደ*

ዘላቂ መፍትሄ የማያሻግሩን ከመሆናቸውም በላይ ዛሬ ባለው የሐገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የትኛውም ወገን አሸናፊ ሆኖ ሊወጣ እንደማይችል ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ የየትኛውም ሃገር ሕገመንግሥት ከጅምሩ 'ሙሉ በኩለሄ' ሆኖ የሚቀረጽ ሳይሆን በሕዝቦች መልካም ፈቃድ ላይ ተመርኩዞ እየበለጸገ የሚሄድ ህያው (organic) ሰነድ መሆን እንደሚገባው መረዳት ይጠቅማል። ባለፉት አምስት ዓመታት ጎልተው የወጡት የፖለቲካ ምስቅልቅሎች እና የእርስ በእርስ ግጭቶች የእንዲህ አይነት ማሻሻያን አስፈላጊነት የሚያመላክቱ ናቸው። ስለዚህም፣ ጊዜው ሳይረፍድ ይህንን ሂደት መጀመሩ ለሁሉም ወገኖች ይጠቅማል።

### *7.2.5 ግራ-የተጋባ ዘመናዊነት*

የዘመናዊነት ጅማሮ በኢትዮጵያ ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይነገራል። እንዳለመታደል ሆኖ፣ የዘመናዊ ትምህርታችን አቀራረጽም ሆነ አሰጣጥ እንዳለ ከውጭ በመገልበጥ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ከእርሱ ጋር የመጣው ዘመናዊነታችንም እንደዚያው ግልብ እና ጥራዝ ነጠቅ እንዲሆን አድርጎታል። በመሆኑም፣ የሩቅ ምሥራቅ ሃገሮች[2] እንዳደረጉት ከምዕራባውያን የሚገኘውን ዕውቀት ከሀገራዊ ሃብታችን እና ማህበራዊ ንዋያችን ጋር በማጣጣም ለዕድገት እና ልማታችን ከመጠቀም ይልቅ በአነጋገራችን[3]፣ አለባበሳችን እና አኗኗራችን እነርሱን ለመምሰል የበለጠ ትኩረት ስንሰጥ ኖረናል። ከዲጂታል መገናኛ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ ባለው ያልተጣራ (unfiltered) የመረጃ ፍሰት ምክንያት እንዲህ አይነቱ ግራ የተጋባ ዘመናዊነት በአዲሱ ትውልድም ላይ በተጠናከረ ሁኔታ በመታየት ላይ ይገኛል።

በዚህም የተነሳ፣ ልንንከባከባቸው የሚገቡን ማህበራዊ እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ ከመሄዳቸውም በላይ ከሌሎች በተሻለ ያሉንን ተፈጥሮአዊ እና ማህበራዊ ንዋዮቻችንንም ሳንጠቀምባቸው ቀርተናል። ይህም እጅግ አሳዛኝ ለሆነ የድህነት እና ኋላቀርነት አዙሪት ዳርጎናል። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ በሚገኝበት አጅግ አሳዛኝ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ደረጃ ሁሉም ያለፉት ተከታታይ መንግሥታት እና ተምረናል የምንለው ትውልዶች ልናፍር ይገባል። ከሁሉም በላይ፣ የአሁኑ ዘመን ወጣት ትውልድ ተመሳሳይ ወጥመዶች ውስጥ

---

[2] ለምሳሌ ያህል ጃፓን፣ ቻይና እና ደቡብ ኮሪያ ያስመዘገቡት እጅግ ፈጣን ዕድገት ከምራባዊያን ሃገራት የቀሰሙትን ዕውቀት ከሃገራቸው ሃገር በቀል ዕውቀት እና ማህበራዊ ንዋይ ጋር በሚገባ በማዋቀናጀታቸው እና ሃገር በቀል ኢንዱስትሪዎችን በማበረታታቸው መሆኑ ይነገራል።

[3] የውጭ ሃገር ቃላቶችን በንግግሮቻችን ውስጥ አለአግባብ መሰንቀር እና የእድሜ እና እውቀት ታላላቆቻችንን በአንቱታ ማክበር የኋላ ቀርነት እና ወግ አጥባቂነት መገለጫ አድርጎ መውሰድ።

እንዳይገባ በመከላከል ያለውን ሁኔታ ለመቀየር በከፍተኛ የቁጭት ስሜት ሊነሳ ይገባዋል። መልካሙ ነገር፣ የአሁኑ ትውልድ ከፈተናዎቹ ባሻገር የቀደምነው ትውልዶች ያልነበሩን እድሎችም ይኖሩታል።

በአሁኑ ወቅት እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እያደገ የመጣው ዲጂታል ቴክኖሎጂ የተለያዩ ፈተናዎች የመደቀኑን ያህል የዕውቀትን ተደራሽነት እና ተወራራሽነት በማፋጠኑ በኩል በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። በዚህ የዲጂታል ዘመን፣ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኝ አንድ ወጣት መሰረታዊ የበይነ መረብ ግንኙነት እና ጽኑ የመማር እና የመፍጠር ፍላጎት እስካለው ጊዜ ድረስ በአጭር ጊዜ በሀገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ይችላል። ለዚህም እንደምሳሌ ሊወሰዱ የሚችሉ በርካታ ወጣቶችን ከዚሁ ከሀገራችን መጥቀስ ይቻላል። ይህንን በማድረግም ለራስም ሆነ ለሃገር የሚተርፍ ሥራ መስራት እንደሚቻል ታይቷል።

ከዚህ በተቃራኒው፣ ከማህበራዊ ሚዲያ ለሚገኙ ጊዜያዊ ጥቅሞች እና ርካሽ እውቅናዎች የበለጠ ትኩረት በመስጠት እና የመንጋ አስተሳሰብ ተከታይ በመሆን ከንቱ ሆኖ መቅረትም ይኖራል። እነዚህን መሰናክሎች ለማለፍ እና የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ኢኮኖሚ ንቁ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ለመሆን ወጣቱ ትውልድ ዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚፈጥራቸውን የመረጃ እድሎች በአግባቡ በመጠቀም እና ልዩ የሆኑ ከባቢያዊ እና ማህበራዊ ንዋዮቻችንን በማበልጸግ ራሱን እና ሃገርን የሚጠቅም ስራ ለመስራት መነሳሳት ይጠበቅበታል። ይህንን በማድረግም ከላይ እስከ ታች ቀስፎ የያዘንን አዕምሮአዊ ድህነት በማስወገድ የራሱንም ሆነ የሀገሪቱን የወደፊት ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደህንነት ማረጋገጥ የሚችል ብቁ ዜጋ መሆን ይችላል።

### *7.2.6 መዋቅራዊ ሙስና*

ለረዥም ዘመናት በሐገራችን በኢትዮጵያ የነበረው ልማዳዊው የፍትህ እና ማህበራዊ አገልግሎት በየአካባቢው በነበሩ የህዝብ ቅቡልነት ባላቸው ሃገር በቀል ሥርዓቶች የሚመራ በመሆኑ ለማንኛውም አይነት ሙስና በር የሚከፍት አልነበረም። ዛሬም ቢሆን ሙስና በሀገር በቀል የፍትህ እና ማህበራዊ አገልግሎት የሚዳኙ ህዝቦች በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚታወቅ አይደለም። ይህ ሁኔታ ግን መንግሥታዊ የፍትህ እና የማህበራዊ አገልግሎት እየተስፋፉ እና ሃገር በቀል የፍትህ እና ማህበራዊ አገለግሎትን እየተካ መሄድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እየተቀየረ መጥቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ እንደ መብት የሚገባንን የመንግሥት አገልግሎት ለማግኘትም ሆነ ከሌሎች ቀድሞ ለመውሰድ በግለሰብ ደረጃ የሚካሄዱ አነስተኛ

ሙስናዎች (petty corruption) እየተስፋፉ መምጣት ጀመሩ። ለእነኚህ አነስተኛ ሙስናዎች መስፋፋት አብዩን ድርሻ የሚያበረክተው ግልጽ በሆነ ተቋማዊ ድክመት ላይ ተመርኩዘው ሃላፊነት የተሰጣቸው ወገኖች የሚፈጥሩት የፍትህ እና ማህበራዊ አገልግሎት እጥረት ነው። የዕለት ተዕለት ኑሮን ለማሸነፍ የሚደረግ ትግልም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይገመታል።

በአንዳንድ ሰዎች ላይ ከሚታይ የአልጠግብ ባይነት ባህርይ ጋር በተያያዘ፣ ከላይ የተጠቀሰውን አነስተኛ ሙስና ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ባይቻልም በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ እንደሚቻል የብዙ ሃገሮች ተሞክሮ ያሳያል። ለዚህ ከሚረዱ አበይት እርምጃዎች አንዱ የመንግሥትን የፍትህ እና ማህበራዊ አገልግሎት ሥርዓት ዘመኑ በሚፈቅደው የመረጃ ቴክኖሎጂ በማሳለጥ የእያንዳንዱን ተቋም የአገልግሎት ብቃቶች በአደባባይ ለህዝብ ዳኝነት ማቅረብ ነው። ሌላው አቢይ እርምጃ መንግሥታዊ አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት ላለባቸው ሠራተኞች ለአገልግሎታቸው እና ለጊዜው ኑሮ የሚመጥን ክፍያ መስጠት እና የተጣለባቸውን የሥራ ሃላፊነት በልዩ ትጋት እና ታማኝነት የሚወጡ ሠራተኞችን ተገቢ እውቅና የሚሰጥ (merit-based) ሥርዓት መዘርጋት ነው። ይህንን የመሳሰሉ እርምጃዎች አቀናጅቶ በመውሰድ በየደረጃው ተንሰራፍቶ ያለውን አነስተኛ ሙስና እና የመልካም አስተዳደር እጦት ችግር በእጅጉ መቀነስ ይቻላል።

ከሁሉም በላይ ግን ባላፉት ሰላሳ እና አርባ ዓመታት አብዛኞቹን የአፍሪካ ሃገሮች ቀስፎ የያዛቸው ችግር የሃገሮችን አንጡራ ሃብት የጥቂት ቡድኖች ወይንም ግለሰቦች መጠቀሚያ ያደረገው መዋቅራዊ ሙስና ነው። ብዙዎቹ የአፍሪካ ሃገሮች ይህንን ችግር ለማስወገድ ጸረ ሙስና ተቋማትን ቢያቋቁሙም ሙስናውን ይበልጥ መዋቅራዊ እንዲሆን ከማድረግ የዘለለ ፋይዳ አላመጡም። በሀገራችን ያለው ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ መዋቅራዊ ሙስና እጅግ ከፍተኛ ደረጃ በሚደርስበት ጊዜ ከሕዝብ አደራ የተቀበለውን መንግሥት ሙሉ ለሙሉ የመቆጣጠር (state-capture) ደረጃ ላይ ይደርሳል። ምንም እንኳን በጥናት በተደገፈ ሁኔታ በሐገራችን ውስጥ ያለው መዋቅራዊ ሙስና መንግሥትን የመቆጣጠር ደረጃ ደርሷል ማለት ባይቻልም ወደዚያው እየተቃረብን መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች[4] እንዳሉ መካድ አይቻልም።

---

[4] በቅርቡ የተደራጀ ሙስና እና ዘረፋ ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለፌደራል መንግሥቱ ስጋት መሆን ደረጃ ላይ መድረሱ በይፋ ተነግሮናል።

ለመዋቅራዊ ሙስና መስፋፋት ከፍተኛውን ድርሻ ያበረከታል ተብሎ የሚታመነው ዋነኛው ምክንያት ሆን ተብሎ በፓርቲ እና በመንግሥት መካከል የሚፈጠር የሚና መደበላለቅ ነው። በሀገራችን እየተጠናከረ የመጣውን መዋቅራዊ ሙስና ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት ይህንን እውነታ በግልጽ ያረጋግጣል። በኢሕአዲግ ዘመን የተወለደው የፓርቲ እና የመንግሥት ሚና መደበላለቅ በብልፅግናም ዘመን ተጠናክሮ በመቀጠሉ መዋቅራዊ ሙስናው በሃገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ደረጃ ላይ ደርሷል። ለዚህ ችግር ዋነኛው መፍትሄው በዘመቻ ግለሰቦችን ማሰር ሳይሆን የተደበላለቀውን የፓርቲ እና መንግስት ሚና በመለየት ለህዝብ ተጠያቂ የሚሆን እና በፓርቲ አባልነቱ ሳይሆን በብቃቱ የሚመዘን መንግሥታዊ ተቋም (civil service) ማደራጀት ነው። ለዚህም ተግባራዊነት በተለይ ወጣቱ ትውልድ በግንባር ቀደምትነት ሊሰለፍ ይገባዋል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ ህመሞች በዋነኝነት ይጠቀሱ እንጂ ሌሎችም መሰረታዊ የአስተሳሰብ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዋናው ቁም ነገር፣ በሃገራዊ ህመማችን ምልክቶች እና ተጓዳኝ መገለጫዎች ላይ መራኮቱን ትተን መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ሂደቶችን መጀመር መቻላችን ነው። ለዚህም የመጀመሪያው እርምጃ ሃገራችን ላለችበት አስዛኝ ሁኔታ መወነጃጀሉን አቁመን የችግሩን መሰረታዊ ምንጮች ለመረዳት እና ለማድረቅ በቁርጠኝነት መነሳታችን ነው። ይህም እውን እንዲሆን፣ ከአሁኑ ወጣት ትውልድ ጉልህ የመሪ ተዋንያንነት ድርሻ የሚጠበቀውን ያህል ቀዳሚ ትውልዶችም በጎ ተሞክሮአቸውን በማካፈል የአዲሱን ትውልድ ጥረት ሊደግፉት ይገባል።

***መደምደሚያ***

*በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው፣ የዚህ መጽሀፍ ዋነኛው መነሻ የእኔን የግል የህይወት ታሪክ መተረክ ሳይሆን በትውልድ ቅብብሎሽ የእያንዳንዳችን ማንነት እንዴት እንደሚቀረጽ ማሳየት እና የዚህም ድምር ውጤት አንድን ሃገር በመገንባትም ሆነ በማፍረስ ያለውን ጉልህ ድርሻ ማመላከት ነው። ይህንንም፣ ምናባዊ በሆነ ፈጠራ ሳይሆን በተጨባጭ እኔው እራሴ ያለፍኩበትን ዋና ዋና የህይወት ጎዳና ከነውጣ ውረዱ እና ስኬቱ በማቅረብ እውናዊ ለማድረግ ሞክሬአለሁ። በዚህ ላይ በመመርኮዝም ባለፉት ስልሳ ዓመታት በሐገራችን የታየውን ቅጥ ያጣ የፖለቲካ ምስቅልቅል መነሻ ምክንያቶች ለማመላከት ተሞክሯል።*

*ባለፉት ዓመታት በርካታ ልሂቃን ሐገራችንን ካለችበት ችግር ለማውጣት መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ደጋግመው ሲናገሩ ተደምጠዋል። የማንኛውም መዋቅራዊ ለውጥ አስኳሉ እና ቀዳሚው ደግሞ የአዕምሮአዊ ውቅር ለውጥ ነው። የዓለማችን ቀደምት ሳይንቲስት አልበርት አይንሽታይን እንዳለው፣* ***'ችግሮቻችንን የፈጠረውን አስተሳሰባችንን ሳንቀይር መፍትሄ ማግኘት አንችልም'*** *እና። በዚህም መሰረት፣ በመጽሀፉ የመጨረሻ ክፍል ካለንበት የፖለቲካ ምስቅልቅል ለመውጣት በእጅጉ የሚያስፈልጉንን አበይት የአዕምሮአዊ ውቅር ለውጦች በሚመለከት ምክረ-ሃሳብ ቀርቧል። ይህንን መርምሮ እና አጣጥሞ ወደ ተግባር በማሸጋገሩ ረገድ የወቅቱ የፖለቲካ መሪዎቻችን እና ልሂቃን የበኩላቸውን ድርሻ ይጫወታሉ የሚል ተስፋ አለኝ።*

*የዚህ መጽሀፍ ዋነኛው ተደራሽ የነገይቱን ኢትዮጵያ መጻኢ እድል በመወሰን ረገድ ቁልፍ ድርሻ ያለው ወጣቱ ትውልድ ነው። ለዚህ ትውልድ ይጠቅማሉ ያልኳቸውን የህይወት ጉዞዬን በግልጽነት ከመተረክ ባሻገር ከተማሪነት፣ ፖለቲከኛነት፣ መሃንዲስነት እና ዲፕሎማትነት ህይወቴ ለወጣቱ ትውልድ ይጠቅማሉ ያልኳቸውን ቁልፍ ምክረ ሃሳቦች በየምዕራፉ መዝጊያ ላይ ለማካፈል ሞክሬአለሁ። ይህ መጽሀፍ የጥቂት ወጣቶችን መጻኢ-ህይወት እና አበርክቶ-ሃገር በበጎ መልኩ መቀየር ከቻለ የመጽሃፉ ዓላማ እንደተሳካ እቆጥረዋለሁ። ይህንን ጽሁፌን አይንሽታይን ለወጣቶች በሰጠው ምክር ለመደምደም፣* ***'ከትናንት ተማሩ፣ ዛሬን ኑሩ፣ ለነገ ተስፋን ሰንቁ፣ ከሁሉ በላይ ግን መጠየቃችሁን አታቁሙ'*** *ለማለት እወዳለሁ።*

አባቴ ፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ ሃላፊነት ወስዶ 'የትውልድ ውርስ' በሚል ርእስ ይሄንን ስራ በማዘጋጀቱ በኔ ትውልድ ስም ከፍተኛ ምስጋና ከአክብሮት ጋር ላቀርብለት እወዳለሁ። የእርሱ የህይወት ጉዞ መታሰቢያ ሆኖ ከማገልገሉም ባሻገር፣ የተለያዩ እሴቶች እና ቁምነገሮችን ያዘለ ስራ በመሆኑ አንባቢው ጠቃሚ ሆኖ ያገኘዋል የሚል እምነት አለኝ። የዚህ ጥረት ውጤት ለእኔ ትውልድ ጠቃሚ ዘር በመሆን መልካም ፍሬ እንደሚያፈራ ተስፋ አደርጋለሁ።

*ዳግማዊ ደስታ መብራቱ*

**ከመጽሃፉ የተወሰዱ**

የዚህ መጽሀፍ ዋነኛው መነሻ የእኔን የግል የህይወት ታሪክ መተረክ ሳይሆን በትውልድ ቅብብሎሽ የእያንዳንዳችን ማንነት እንዴት እንደሚቀረጽ ማሳየት እና የዚህም ድምር ውጤት አንድን ***ሃገር በመገንባትም ሆነ በማፍረስ*** ያለውን ጉልህ ድርሻ ማመላከት ነው።

*****

ወላጆቻችን ከአያት ከቅድም አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ለነፃነት ቀናኢነት እና አልበገርም ባይነት ከልጅነት እስከ ዕውቀት ኖረውት ጥብቅ የሆነ የሃገር መውደድ ስሜትን አውርሰውናል። በስጋ ከሚወለዷቸው ባልተናነሰ የሚያፈቅሯቸው እህቶች እና ወንድሞች በማፍራት፣ 'መወለድ ቋንቋ ነው' የሚለውን ሃገራዊ ብሂል በተግባር ኖረው ***ሰፊ ማህበራዊ ትስስርን አስተላልፈውልናል***።

*****

በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ***ወጣቱ ትውልድ ቀዳሚ የለውጥ አራማጅ*** እንደሚሆነው ሁሉ እኔም እንደዚያ የ1960ዎቹ ትውልድ በ1966ቱ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ተሳትፌአለሁ። ይህ ተሳትፎዬ በወቅቱ ውድ ዋጋ ቢያስከፍለኝም፣ የዚህ አካል በመሆኔ ከፍተኛ ደስታ እና እርካታ ይሰማኛል።

*****

ባለፉት ዓመታት በርካታ ልሂቃን ሐገራችንን ካለችበት ችግር ለማውጣት መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ደጋግመው ተናግረዋል። የማንኛውም መዋቅራዊ ለውጥ አስኳሉ እና ቀዳሚው ደግሞ የአዕምሮአዊ ውቅር ለውጥ ነው። የዓለማችን ቀደምት ሳይንቲስት አልበርት አይንሽታይን እንዳለው፣ ***ችግሮቻችንን የፈጠረው አስተሳሰባችንን ሳንቀይር መፍትሄ ማግኘት አንችልም*** እና።

ISBN 978-99990-50-

ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር

+251 11 56 52 52

ብር፡ 350 USD 20.00